# በአውቶቡስ ስለመጓዝ ማወቅ ያለብዎት ነገር

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከዚህ እንደሚከተለው የአውቶቡስ አገልግሎት ይሰጣል፦

- * ከትምህርት ቤታቸው በእግር ጉዞ 1 ማይል በላይ ርቀው ለሚኖሩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች።
- * ከትምህርት ቤታቸው በእግር ጉዞ 1.5 ማይል በላይ ርቀው ለሚኖሩ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች።
- * ከትምህርት ቤታቸው በእግር ጉዞ 2 ማይል በላይ ርቀው ለሚኖሩ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች
- * በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትራንስፖርት መምሪያ እንደተደነገገው ከትምህርት ቤት ርቀት ባሻገር (ብዙ አውራ መንገዶች፣ የግንባታ ቦታዎች፣ ወዘተ) አስቸጋሪ የእግር ጉዞ ሁኔታዎች ለሚያጋጥማቸው ተማሪዎች።
- * ልዩ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች፣ ማግኔት፣ ምጡቅ ተሰጥኦ ያላቸው፣ እና በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት የማይሰጡ አንዳንድ የሙያ ትምህርት ፕሮግራሞች።

* የተመጣጠነ ርቀት ለመወሰን የአንድ ማይል አንድ አስረኛ (1/10) ሊጨመር ይችላል።

## ተማሪዎች

ተማሪዎች በማንኛውም ጊዜ በት/ቤት አውቶቡስ ውስጥ እና በት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያዎች ላይ በሚጠብቁበት ጊዜ ሁሉ ስለባህሪያቸው ራስን የመግዛት ሃላፊነት አለባቸው። የተዛባ የተማሪዎች ባህርይ የአውቶቡስ ኦፕሬተሩ ከቤት ወደ ት/ቤት እና ከት/ቤት ወደ ቤት በሚያሽከረክርበት ጊዜ በማዘናጋት የሁሉንም ተሣፋሪዎች ደህንነት የሚያሰጋ እና የማያስደስት አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ። ተማሪዎች የመምህራንን እና የት/ቤት አስተዳዳሪዎችን መመሪያ እንደሚከተሉ ሁሉ የአውቶቡስ ኦፕሬተርን መመሪያ ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

## ወላጆች

ወላጆች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ሥርዓታማ እና አስደሳች የአውቶቡስ ጉዞዎችን ለማረጋገጥ የአውቶቡስ ሕጎችን እና መጠበቅ ያለባቸውን የሥነ ምግባር ደንቦች ልጆቻቸው እንዲያውቁ በማድረግ የሁሉንም ተማሪዎች ደህንነት የበለጠ ማገዝ ይችላሉ።ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና ለመለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ ወላጅ ወይም ሌሎች ጎልማሳ ሰዎች ከተማሪዎቹ ጋር በት/ቤት አውቶቡስ ፌርማታ ላይ አብረው እንዲቆዩ እና ባህሪያቸውን እንዲቆጣጠሩ፥ እና በማናቸውም ችግር ጊዜ ለምሳሌ፦ የአውቶቡስ ዘግይቶ መድረስ፥ በመሣሰሉት ጊዜያት እንዲረዷቸው ይመከራል።

አብዛኛዎቹ የአውቶቡስ መስመሮች የተነደፉት ተማሪዎች የት/ቤት አውቶቡስ ለመሣፈር አውራ መንገዶችን እንዳያቋርጡ ተደርጎ ነው። ይህ የአውቶቡስ መስመር መግለጫ "RSO" ላይ (በቀኝ በኩል ብቻ) ከአውቶቡስ ማቆሚያ ምልክት ቀጥሎ ተገልጿል። ሌላ ፌርማታ ካለ ወላጆች ልጆቻቸው ሌላ የአውቶቡስ ማቆሚያ ለመጠቀም ብለው ለደህንነታቸው ስጋት እንዳይሆን መንገድ ማቋረጥን መፍቀድ የለባቸውም። መንገድ ሳያቋርጡ በእነርሱ በኩል ምንም የአውቶቡስ ማቆሚያ የሌለ ከሆነ ወላጆች የዴፖ ማኔጀር ማነጋገር አለባቸው

## ማህበረሰብ

ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ወደ አውቶቡስ ማቆሚያ ለማድረስ፣ በት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ቦታ፣ እና ከአውቶቡስ ማቆሚያ ወደ ቤት ሲሄዱ ልጆቻቸውን የመጠበቅ ሃላፊነት አለባቸው። ልጆች ከተመደበላቸው የመሣፈሪያ ሰዓት ቢያንስ 5 ደቂቃ በፊት በአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታቸው መድረስ አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ከሰአት በኋላ ልጆቻቸውን ለመቀበል ሠዓት ጠብቀው የት/ቤት አውቶቡስ ፌርማታ ላይ የመድረስ ሃላፊነት አለባቸው፥ እና በሠዓቱ አውቶቡሱን ለማግኘት ማቀድ፣ ተንከባካቢ ወይም ሌላ ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው ልጆቹን ወደ ቤታቸው ወይም የህጻናት እንክብካቤ ወደሚሰጥበት ቦታ በደህና እንዲደርሱ ማዘጋጀት አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ከአውቶቡስ የቱ ጋ እንደሚወርዱ ማስተማር፥ እና ለመጀመርያ ጊዜ አውቶቡስ ከመሳፈራቸው በፊት ልጆች ከአውቶቡስ የሚወርዱበትን ቦታ በትክክል እንዲያውቁ፣ ከአውቶቡስ መቆሚያ ሥፍራ ወይም ምልክቶች ልዩ ሁኔታ ጋር በደምብ እንዲላመዱ ማስተዋወቅ አለባቸው።

**እባክዎ ልብ ይበሉ፦የአውቶብስ ኦፕሬተሮች በማንኛውም ቀን ልጆቹን መረከብ የሚችሉ ሁሉንም ሰዎች ለይተው ላያውቁ ይችላሉ፣ እናም እያንዳንዱን ልጅ ከሚቀበላቸው አዋቂ ሰው ጋር ማገናኘት አይችሉም።ተማሪዎች ከአውቶቡስ ሲወርዱ፣ ሙሉ በሙሉ**

**በወላጅ/አሳዳጊ ወይም በሌላ ተንከባካቢ ቁጥጥርና ኃላፊነት ውስጥ ናቸው። ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ ከሌለ ወደ ቤታቸው የሚሄዱት ብቻቸውን ነው።**

በትምህርት ቀናት ብዙውን ጊዜ ልጅዎን ከት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ የሚቀበሉ ከሆነ፥ ነገር ግን በሆነ ቀን ይህን ማድረግ ካልቻሉ፣ ከትምህርት ቤት የመውጫ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ደውለው ልጅዎ አውቶቡስ ላይ እንዳይሳፈር/እንዳትሳፈር በትምህርት ቤት እንዲቆይ/እንድትቆይ እና መጥተው እንደሚወስዱ መንገር አለብዎት።

በመጀምርያው ሳምንት የሙአለህፃናት መምህር ስለ አውቶብስ ደህንነት በዝርዝር ይገልጽልዎታል። አውቶቡስ በመሳፈር ፣ በመጓዝ፣ እና ከአውቶቡስ በሚወርዱበት ጊዜ የደህንነት ህጎችን ማክበር አስፈላጊ ነው። የደህንነትን ህጎች ከልጅዎ ጋር ሆነው መገምገም የአውቶቡስ ጉዞ ደህንነትን ለማረጋገጥ ያግዛል።

ልጅዎ ከሰዓት በኋላ ከት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ወደ ቤት በእግሩ/ሯ ሲጓዝ-ስትጓዝ አዋቂ ሰው አብሮ እንዲሆን የሚፈልጉ ከሆነ፥ የሚከተለውን እንዲያደርጉ እናሳስባለን፦

- አውቶቡሱ በማንኛውም ቀን ቀደም ብሎ መድረስ ስለሚችል፣ እርስዎ ወይም ሌላ ሰው ከመደበኛ የመድረሻ ሰዓት አስቀድሞ ለመገኘት ማቀድ አለብዎት።
- እርስዎ የማይገኙ ከሆነ እርስዎን በመተካት ሌላ አዋቂ ሰው የት/ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ ላይ በመድረስ ልጅዎን እንዲረከብ/እንድትረከብ በቅድሚያ ያዘጋጁ።
- አስቸኳይ ሁኔታ ቢያጋጥምዎትና አውቶቡስ ጣብያ ለመድረስ የማይሳካልዎት ከሆነ፣ ልጅዎ አውቶቡስ ላይ ከመሳፈር ይልቅ ከት/ቤት መጥተው እንዲወስዱ በት/ቤት እንዲቆይ/እንድትቆይ ከመሰናበቻ ሰአት በፊት አስቀድመው ወደ ት/ቤቱ ደውለው መንገር አለብዎት። ለአስቸኳይ ሁኔታ የት/ቤቱ ቴሌፎን ቁጥር ሁልጊዜ ከርስዎ ጋር እንዳለ ያረጋግጡ።
- ልጃችሁ ተገቢውን የት/ቤት አውቶቡስ መቆሚያ መለየቱ(ቷ)ንና ሌላ መቆሚያ ላይ ከአውቶቡሱ መውረድ እንደሌለበ(ባ)ት መገንዘቡ(ቧ)ን ያረጋግጡ።
- አንድ ትልቅ ተማሪ "ጓደኛ" ከልጅዎ ጋር ወደ ቤት እንዲሄድ ወይም መውሰድ እስከሚችሉ ድረስ ልጅዎ በትልቁ(ቋ) ተማሪ መኖሪያ ቤት እንደሚቆይ/እንደምትቆይ ያመቻቹለ(ላ)ት። ይህን ሲያቅዱ ከሌላው(ዋ) ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ጋር አብራችሁ ተነጋግራችሁ መሆን አለበት።
- አንድ ነገር "ትክክል ካልሆነ"፣ ልጅዎ ከአውቶቡስ ከመውረዱ/ዷ በፊት ለአውቶቡስ አሽከርካሪ መንገር እንዳለበ(ባ)ት ማወቁ(ቋ)ን ያረጋግጡ። ይህ ማለት አብዛኛውን ጊዜ በት/ቤት አውቶቡስ መቆሚያ ላይ የሚገኝ/የምትገኝ አሁን ግን በአውቶቡስ ማውረጃ ቦታ ላይ ካልተገኘ (ች)፥ ወይም መቆሚያውን ከሳተ(ች)፥ ወይም በስህተት ሌላ አውቶቡስ ላይ ከተሳፈረ(ች) እና ማንኛውንም መውረጃ ቦታ ካላወቀ(ች) ወይም የሚታወቅ አዋቂ ሰው ያለማግኘትን ያካትታል።

**ተማሪው(ዋ) አንዴ ከአውቶቡስ ከወረደ(ች) በኋላ፣ክትትል ማግኘቱ(ቷ)ን ማረጋገጥ የሚችሉት እርስዎ ብቻ ነዎት።**

## በአውቶቡስ ማቆሚያ፣ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፦

- ከተመደበው ጊዜ 5 ደቂቃ በፊት ይድረሱ።
- ሳይገፋፉና ሳይጨናነቁ ወደ አውቶቡሱ በፍጥነት ለመሳፈር እንዲችሉ ለመዘጋጀት በሥርዓት መስመር ይያዙ።
- ከመንገድ ርቀው ይቁሙ።
- በአቅራቢያ ላሉ መስኮች፣ የመኪና መንገዶች፣ ቤቶች፣ ህንፃዎች እና የግል ንብረቶች ጥንቃቄ ያድርጉ።
- ወደ አውቶቡሱ መግባት ያለባቸው በትክክል ከቆመ በኋላ እና አሽከርካሪው(ዋ) ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ምልክት ከተሰጣቸው በኋላ ብቻ ነው።

## በአውቶቡስ ውስጥ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፦

- ልክ በክፍል ውስጥ እንዳሉ ሁሉ ተገቢውን ባህሪ መጠበቅ አለባቸው።
- መተላለፊያ ቦታ እና የድንገተኛ መውጫውን በር ከሚያደናቅፉ ነገሮች ነጻ መሆን አለበት።
- እጃቸውን፣ እግሮቻቸውን እና ጭንቅላታቸውን ሁል ጊዜ በአውቶቡሱ ውስጥ ያቆዩ።
- መቀመጥ አለባቸው እና ለሌሎችም እንዲቀመጡ ቦታ ይስጡ። በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ አንድ ጊዜ አሽከርካሪዎች ካስተካከሉ በኋላ አውቶቡሱ ሲንቀሳቀስ መቆም አይፈቀድም።
- ቆሻሻ ነገሮችን በተገቢው የቆሻሻ መጣያ ላይ ያስወግዱ።

## ተማሪዎች ወደ ቤት በሚመለሱበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፦

- ከቆመው አውቶቡስ ፊት ለፊት በእግር ሲራመዱ10 ጫማ ርቀው መሆን አለበት፣ መንገድ መሻገር ካለባቸው የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ካረጋገጠላቸው በኋላ ብቻ ይሻገሩ።

- ከአውቶቡስ ሲወጡ ትራፊኩን ለመምራት ከመሞከር ይቆጠቡ።

***በማንኛውም ጊዜ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ የለባቸውም፡-***

- እንስሳትን፣ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ትምባሆ፣ የጦር መሳሪያዎችን፣ ከብርጭቆ መስታወት የተሠሩ እቃ መያዣዎችን ወይም ፊንጂዎችን ይዘው በአውቶቡሱ ውስጥ መግባት አይፈቀድም።
- ጸያፍ ቃላትን ወይም ምልክቶችን መጠቀም፣ መታገል/መላፋት፣ ወይም ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆነ እና/ወይም ህገወጥ ድርጊት ውስጥ መሳተፍ ክልክል ነው።
- ማንኛውንም ወረቀቶች ወይም ቆሻሻዎችን በአውቶቡስ ውስጥ ወይም በመስኮት መጣል አይፈቀድም።
- ድንገተኛ ካልሆነ በስተቀር የአደጋ ጊዜ መውጫዎችን ያለፈቃድ መክፈት ክልክል ነው።
- በአውቶቡስ ውስጥ እያሉ ያለጆሮ ማዳመጫ ሬዲዮ/ሙዚቃ ማጫወት፣ ማጨስ፣ መጠጣት፣ወይም መብላት አይፈቀድም።
- የአውቶቡሱን ማንኛውንም ቦታ ማበላሸት ክልክል ነው።
- ከወላጅ የጽሁፍ ፈቃድ ከሌላቸው እና ከርእሰመምህር ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር ከተመደቡበት በተለየ የት/ቤት አውቶቡስ መጓዝ አይችሉም።